# ሰሞነኛው የፀረ-ሙስና እርምጃና ጥላሸት ቀቢዎቹ

**ጀማል ኑሩ 05/18/13**

ታላቁ መሪያችን አቶ መለስ ዜናዊ በህይወት በነበሩበት ወቅት የሙስና ወንጀልን አስከፊነት አስመልክተው "የኢትዮጵያን የዕድገት ግስጋሴ አንድ ጋት እንኳን ወደ ኋላ ለመጎተት የሚሞክሩ የሀገርና የህዝብ ጠላት ናቸው" በማለት ደጋግመው ይናገሩ እንደነበር አስታውሳለሁ። እርግጥም እኚህ ባለ ራዕይ መሪ በየጊዜው ይህን ሃቅ ሳያሰልሱ ይናገሩ የነበሩት ያለ ምክንያት አልነበረም–የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ ምን ያህል የሀገርንና የህዝብን ተጠቃሚነት በመሸርሸር የህልውና አደጋ ሊሆን እንደሚችል ለማመላከት እንጂ።

አዎ! የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ የሀገራችንን ነፃ ገበያ ሥርዓት እየተፈታተነው ብቻ ሳይሆን አስተሳሰቡን ለማራመድ የተዘረጉት እጆች ሊሰበሰቡ ባለመቻላቸው፣ አደጋው ምጣኔ ሐብታችን አሁን ካለው ፍጥነት በተሻለ ሁኔታ እንዳያድግ ብሎም ለፀረ- ዴሞክራሲያዊነት በር የሚከፍት ሁኔታን ሲፈጥር መቆየቱ የሚዘነጋ አይደለም፡፡ ታዲያ ይህን አደገኛ ሁኔታን በአንክሮ የሚከታተለው መንግስት ድርጊቱ የስርዓቱ አደጋ መሆኑን ከላይ በመግቢያዬ ላይ በጠቀስኩት መልኩ ደግሞ ደጋግሞ ሲገልፅ እንደነበርም እናስታውሳለን። ይህን ሀገራዊ አደጋ ከመግለፅ ባለፈ በተለይም በ1993 ዓ.ም በተካሄደው የተሃድሶ እንቅስቃሴ ወቅት የኪራይ ሰብሳቢነት መገለጫ አንዱ በሆነው ሙስና ላይ የመጀመሪያውን ተግባራዊ ክንዋኔ በወቅቱ የመከከላከያ ሚኒስትር በነበሩት በአቶ ስዬ ኣብርሃ እና በሌሎች ባለስልጣናት ላይ ገቢራዊ ማድረጉ ይታወቃል። ይህም በየትኛውም ደረጃ የተቀመጠ ማንኛውም የመንግስት ባለስልጣን ስልጣኑን መከታ በማድረግ ከህግ ተጠያቂነት ሊያመልጥ የማይችል መሆኑን በግልፅ ያመላከተ ጉዳይ ነው።

ታዲያ ይህን የማይናወጥ የመንግስት አቋምን በመመስረት ፣ ሰሞኑን የፌዴራሉ ስነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ጋር በመቀናጀት፣ በከባድ የሙስና ወንጀል የጠረጠራቸውን የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናትን ጨምሮ 25 ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር በማዋል ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እንዲታይ እያደረገ መሆኑ ይታወቃል። እርግጥ ይህ ተግባር መንግስት ዛሬም ቢሆን እንደ ትላንቱ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የዜጎቹን መብትና ጥቅም ለማስከበር ያለውን ፅኑ እምነትና ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው።

ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው፤ የሙስና ተግባር የተወሳሰበና ጊዜን የሚጠይቅ ቀጣይ ትግል በመሆኑ ሳቢያ መንግስት በየጊዜው ከህዝቡ የሚቀርቡለትን የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለመፍታት ቃል ሲገባ ቆይቷል። እናም እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ይህ እርምጃው ለህዝቡ የሰጠው ምላሽ አካል ይመስለኛል። ግና "በጥባጭ እያለ ማን ጥሩ ይጠጣል" እንዲሉ አበው፤ መንግስት በራሱ ተጠርጣሪ ከፍተኛ ባለስልጣናት ላይ ሳይቀር የወሰደውን ይህን የተቀደሰ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ፤ አንዳንድ ወገኖች 'ለምን በሙስና የተጠረጠሩ ባለ ስልጣናትና ግለሰቦች ተያዙ?' በሚመስል መልኩ በአሳፋሪ ሁኔታ የመንግስትን ስም ጥላሸት ለመቀባት ሲጠቀሙበት አስተውያለሁ።

እነዚህ ወገኖች 'እነ እገሌ በቁጥጥር ስር የዋሉት በሙስና ሳይሆን በፖለቲካ አነሳሽ /politically motivated / ምክንያት ነው' እንዲሁም 'መንግስት እስካሁን ምን እየሰራ ነበር፣ ትላንት በሙሰኞች ላይ ለምን አልተነሳም?' የሚሉ ጥንቀላ መሰል ብሎም ኢ-ምክንያታዊ የሆኑ ጥያቄዎችን በማንሳት የመንግስትን ሰናይ እንቅስቃሴ ለማጥላላት ሞክረዋል። እኔም ይህን ፅሑፍ ለማሰናዳት ምክንያት የሆነኝ የእነዚሁ ወገኖች መሰረተ-ቢስና በጥላቻ ላይ የተመሰረቱ አስተሳሰቦች መሆናቸውን ውድ አንባቢዎቼ እንዲገነዘቡልኝ እፈልጋለሁ። እናም ሁሉም ሊባል በሚችል ደረጃ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያገኘውን የሰሞኑን የፀረ-ሙስና እርምጃንና አንድምታውን በማሳየት፤ ለጥቂ ደግሞ ከራሳቸው ድብቅ ፖለቲካዊ አጀንዳ በመነሳት የመንግስትን ተመስጋኝ እንውስቃሴ ለማጥላላት ሆን ብለው በጉዳዩ ላይ "ጭቃ ለመለጠፍ" የሚቧችሩትን ጨለምተኛ ግለሰቦች የተወላገዱ አስተሳሰቦችን ለማረቅ እሞክራለሁ።

ውድ አንባቢዎቼ እንደሚያውቁት፤ በሀገራችን ውስጥ የተመሰረተው ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአስተማማኝ ሁኔታ ቀጥሎ መላውን ህዝብ በየደረጃው በሁሉም መስኮች ተጠቃሚ ማድረግ ይችል ዘንድ፣ የስርዓቱ እንዲሁም የህዝብና የሀገር ጠላት የሆነው የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ ከመሰረቱ መናድ ይኖርበታል። ሁላችንም እንደምንረዳው ኪራይ ሰብሳቢነት የመንግስት ስልጣንን በመጠቀም ከባለ ስልጣኖች ጋር ተሳስሮ በገበያ ውድድር ሊገኝ ከማይችለው በላይና ውጪ ትርፍ የሚገኝበት የስራ መስክ ነው፡፡ እርግጥ አንዳንድ ግለሰቦች ኪራይ ሰብሳቢነትን ከዘረፋ ጋር በቀጥታ ያገናኙታል፡፡ ለነገሩ ዘረፋን ከኪራይ ሰብሳቢት ለይቶ መመልከት አስቸጋሪ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም አንድ ግለሰብ ሊኖረው የሚችለው የመዝረፍ ዕድል ሌላውም በእኩልነት ሊያገኘው አይችልም፡፡ በመሆኑም በዚህ የሀገርን ኢኮኖሚ የኋሊት ሊጎትት የሚችል የዘረፋ ዓለም ውስጥ የጥሎ ማለፍ ውድድር ካልሆነ በስተቀር፣ ሁሉም ከዘረፋው እኩል ተጠቃሚ የሚሆንበት ሥርዓት ሊዘረጋ አይችልም፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ ሁሉም እኩል ይዝረፍ እያልኩ እንዳልሆነ አንባቢዎቼ እንዲገነዘቡልኝ እሻለሁ፡፡

ይሁንና የኪራይ ሰብሳቢነት ሥርዓት የዜሮ ድምር ጨዋታ (zero sum Game) ነው የሚለውን የበርካታዎችን ሃሳብ ግን እጋራለሁ፡፡ ለምን ቢሉ ሀገራችን በአሁን በምትገኝበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ልዩነትን በሠላማዊ መንገድ መፍታት፣ መቻቻልን መሰረት ማድረግ እንዲሁም አንዱ ሲያገኝ ሌላው በልማታዊ ውጤቱ መጠን የሚያገኝበት ሁኔታ በመኖሩ ነው፡፡ ዳሩ ግን በዜሮ ድምር ውጤት አሰላለፍ ፣ አንዱ ሲያገኝ የሌላው የማግኘት መብት በዚያው መጠን ይዘጋል፡፡ እናም በዚህ የጥሎ ማለፍ ውድድር ውስጥ መቻቻል የሚባል ነገር ከቶውንም ሊታሰብ አይችልም፡፡ ታዲያ ውድድሩ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓታችን ውስጥ የተንሰራፋ ከሆነ፣ ፖለቲካው ራሱ የዜሮ ድምር ጨዋታና ፀረ- ዴሞክራሲያዊ ከመሆን የዘለለ ዕጣ ፈንታ ሊኖረው የሚችል አይመስለኝም፡፡ በመሆኑም በዴሞክራሲያዊ ሥርዓታችን ውስጥ እንዲህ ዓይነቱ የዜሮ ድምር ውጤት የጥሎ ማለፍ ውድድር እንዲዘጋ፣ በአስተሳሰቡ ውስጥ ያሉ ግለሰቦች እጆቻቸው ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

ለዚህ አባባሌ አሳማኝ ማስረጃ ማቅረብ እችላለሁ። ይኸውም የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ - ኢኮኖሚ በሌለበት ነፃ የገበያ ሥርዓት፣ እያንዳንዱ ሰው በልማት ውጤቱ መጠን ሀብት የሚያፈራበት ሁኔታ ሊኖር የሚችል መሆኑ ነው፡፡ ሀብት፣ ጉልበትና ዕውቀት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በልማቱ ላይ እነዚህን አቅሞቻቸውን በላቀ ሁኔታ በተጠቀሙበት መጠን ተጠቃሚነታቸው መረጋገጡ አይቀሬ ነው፡፡ እዚህ ላይ ሁሉም ሰው በልማቱ ላይ ባዋለው ዕውቀት፣ ጉልበትና ሀብት መጠን እኩል ሀብት የማፍራት ዕድል እንዳለው መገንዘብ ያስፈልጋል። እርግጥ በዕድሉ በላቀ ደረጃ የተጠቀመ ሰው የተሻለ ገቢ ማግኘቱ አይቀርም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ ከነጻ ገበያ ሥርዓት አንጻር ሲመዘንም፣ ፍትሃዊነቱ አጠያያቂ አይሆንም፡፡ የኪራይ ሰብሳቢነት ፀረ - ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ግን በመርሆዎች ላይ በመስማማት ሊሰራ ስለማይችል፣ ያለው አማራጭ የመጠቃቀም ሰንሰለቶችን (Patronage networks) ከላይ እስከ ታች ድረስ በመፍጠርና ደጋፊን በማብዛት ዝርፊያውን ማጧጧፍ ነው— ምንም እንኳን ጠብ የሚል ነገር ለማያገኘውና ታች ላለው አብዛኛው ህዝብ ነገሩ "ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ" እንዲሉት ዓይነት ቢሆንበትም፡፡ (ታዲያ እዚህ ላይ ውድ አንባቢዬ ሰሞኑን የፀረ-ሙስና ኮሚሽን መርማሪ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንን የሙስና ተጠርጣሪዎች ጉዳይ በሶስት ቦታ ከፋፍለው በየክሱ መዝገብ ስር የደረደሯቸውን ግለሰቦች ልብ ይሏል!...)

እናም ከዚህ ነባራዊ ዕውነታ በመነሳት የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ- ኢኮኖሚ የበላይነት በሰፈነበት ሀገር ውስጥ ዴሞክራሲን ማሰብ፣ በምድረ -በዳ ላይ እህል ዘርቶ የተለየ ውጤት የመጠበቅ ያህል መሆኑን የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘብልኝ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ምክንያቱም ዴሞክራሲን ለማቋቋም ቢታሰብ እንኳን፣ ዴሞክራሲው ፍሬ የሚያፈራ፣ ዘላቂነት የሌለው እንዲሁም በዴሞክራሲ ሽፋን በተለያዩ የመጠቃቀም ትስስሮች መካከል የሚካሄድ የኪራይ ሰብሳቢዎች

ፍልሚያ ከመሆን የዘለለ ፋይዳ ይኖረዋል ተብሎ ስለማይታሰብ ነው፡፡ ስለሆነም በሀገራችን ውስጥ ዴሞክራሲን በተሟላ ሁኔታ ለማስፈን የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብን ማምከን ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አለመሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ ሀገራችን እንደ ህልውና ጉዳይ የያዘችውን ከድህነት የመውጣት ራዕይዋን የሚያሰናክል አሜኬላ እሾህ ከመሆን በዘለለ፣ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባህል ግንባታችን ላይ የሚፈጥረው አደጋ እጅግ ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘቧ ነው። ለዚህም ይመስለኛል መንግሰት ከዚህ ሀገራዊ የህልውና ጉዳይ አንድምታ በመነሳት ኪራይ ሰብሳቢነትን በአጠቃላይ፣ ሙስናን ደግሞ በዋነኛነት በመዋቅሩ ውስጥ የሚገኙት የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎቶች ሁለንተናዊ ሁኔታን ተላብሰው ግልፅነት፣ ተጠያቂነትና የህዝብ አገልጋይነት እንዲሰፍን በመታገል የሰሞኑን ዓይነት እርምጃ የወሰደውና ወደፊትም ለመውሰድ ቁርጠኝነቱን በማገለፅ ላይ የሚገኘው።

እንግዲህ ውድ አንባቢዎቼ መንግስት ሰሞኑን ያካሄደው የፀረ-ሙስና እርምጃ ቀደም ሲል ከጠቀስኩት ሀገራዊ የሞት ሽረት አንድምታ አኳያ የተከናወነ መሆኑን ከተገነዘባችሁልኝ ዘንዳ፣ እስቲ አሁን ደግሞ አንዳንድ ጨለምተኛ ግለሰቦች ‘እነ እገሌ በቁጥጥር ስር የዋሉት በሙስና ሳይሆን በፖለቲካ አነሳሽ /politically motivated/ ምክንያት ነው’ እንዲሁም ‘መንግስት እስካሁን ምን እየሰራ ነበር?፣ ትላንትስ በሙሰኞች ላይ ለምን አልዘመተም?’ በማለት አስመስጋኙን እንቅስቃሴ ሆን ብለው ጥላሸት ለመቀባት በመደስኮር ያናፈሷቸውን የጥላቻ ዘመቻን እንመልከት።

በመጀመሪያ ደረጃ ሰሞኑን በቁጥጥር ስር የዋሉት የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት ከላይ በጠቀስኩት በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው እንጂ ጨለምተኞቹ እንደሚያራግቡት በፖለቲካ አነሳሽነት ምክንያት አለመሆኑን ከሁለት ነባራዊ ሃቆች አኳያ በመመልከት መረዳት ያስፈልጋል። አንደኛው በጉዳዩ ዙሪያ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚሰጠው መላ-ምት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የሀገራችን የፀረ-ሙስና ትግል ከፖለቲካ ልዩነት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌለው መሆኑ ነው።

እንደሚታወቀው በየትኛውም ሀገር ውስጥ የመንግስት ባለስልጣናት አሊያም የተቃዋሚ ቡድን አመራሮች በሙስና ተጠርጥረው ሲያዙ በቅድሚያ የሚሰነዘረው መላ-ምት ግለሰቦቹ የተያዙት በፖለቲካ ልዩነታቸው ምክንያት ነው የሚል ነው። ለአብነት ያህል በቅርቡ የቦስኒያ መንግስት አቃቤ ህግ የሀገሪቱን ፕሬዚዳንት ዝቪኮ ቡድሚርን በሙስና ወንጀል ጠርጥሮ እንዲከሰሱ ሲደርጋቸው፣ በርካታዎች የሰነዘሩት መላ ምት የጉዳዩ ድምፀት ፖለቲካዊ እንጂ የሙስና ጉዳይ አይመስልም የሚል ነበር። ሌላም ምሳሌ ላክል። የ71 ዓመቱ የኒጀሩ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ ማሐማዱ ኢሶፉ በሀገሪቱ መንግስት በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው ሲከሰሱና ከሀገር እንዳይወጡ ሲታገዱ እርሳቸውና ፓርቲያቸው ያቀረቡት ምክንያት ክሱ ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ነው የሚል ነው።

እንግዲህ እነዚህ ጥቂት አብነቶች የሚያሳዩን ነገር ቢኖር የመንግስት ባለስልጣናት አሊያም ተቃዋሚዎች በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው ክስ ሲመሰረትባቸው ጉዳዩ 'ከፖለቲካ ጋር የተያያዘ ነው' ማለት የተለመደ መከራከሪያ መሆኑን ነው። ለዚህም ነው የፌዴራሉ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ዓሊ ሱሌይማን ሰሞኑን ከጋዜጠኞች ለቀረበላቸው ጥያቄ 'ጉዳዩ በሀገራችን ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሀገሮችም የመንግስት ባለስልጣናት ሲያዙ ጉዳዩ ፖለቲካ ነው መባሉ አይቀርም' በማለት ሃቁን ለማሳየት የሞከሩት። ለነገሩ ይህ ጉንጭ አልፋ መከራከሪያ ወደፊት በፍርድ ቤት ሊረጋገጥ  የሚችል በመሆኑ ከወዲሁ በጉዳዩ ላይ አስተያየት መስጠት አግባብነት ያለው አይመስለኝም። የኢትዮጵያን መንግስት ስም ለማጥፋት የተሰለፉት ወገኖችም በፍርድ ቤት የተያዘን ጉዳይ "ወጡ ሳይወጠወጥ፣ ወስከንቢያው ቂጢጥ" እንዲሉ አስቀድመው 'የፖለቲካ ጉዳይ ነው' እያሉ መዘላበዳቸው ሁሉንም ነገር የማጥላላት አባዜ የተጠናወታቸው መሆናቸውን በራሳቸው እጅ በገሃድ ማንነታቸውን ከማጋለጥ በስተቀር የሚያስገኝላቸው አንዳችን ፋይዳ የለም።

ያም ሆነ ይህ ግን የመንግስትን ስም ለማጉደፍ 'እነ እገሌ የታሰሩት በፖለቲካ ልዩነታቸው ምክንያት ነው' የሚለው የማጥላላት ዘመቻ፤ ሀገራችን የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማካሄድ ከተነሳችበት ተጨባጭ ሀገራዊ ምክንያት አኳያም በፍፁም ተቀባይነት የሌለው ነው። እዚህ ሀገር ውስጥ የምንኖር ሰዎች እንደምናውቀውም ይሁን የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ተደምመው እንደመሰከሩት በልማታዊውና ዴሞክራሲያዊው መንግስት አማካኝነት በተቀረፁትና ትክክለኛነታቸውን በተግባር ያረጋገጡት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ሀገራችንን ላለፉት ስምንትና ዘጠኝ ዓመታት በፈጣንና ተከታታይ ዕድገት ውስጥ እንድትገባ እንዲሁም ህዝቦቿ በየደረጃው ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስችለዋል። ይህ ልማታዊ ዕድገት ካመጣቸው በርካታ ትሩፋቶች ውስጥ አንዱ ከፍተኛ ገንዘብ በመንግስት ተቋማትም ይሁን በግለሰቦች እጅ ውስጥ የመዘዋወር ዕድል መፍጠሩ ነው። ታዲያ ይህን ከፍተኛ የገንዘብ ዝውውርን በአግባቡ መምራትና ማስተዳደር ካልተቻለ፤ ያልተሰበሱት ኪራይ ሰብሳቢ እጆች እንዲረዝሙ ክፍተት መፈጠሩ አይቀሬ ነው። እናም ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ለኪራይ ሰብሳቢዎች ምቹ ምህዳርን ባለመፍጠር የሀገርንና የህዝብን ሃብት ከምዝበራ ለማዳን ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ መብት፣ ግዴታና ኃላፊነቱን መወጣት ይኖርበታል።

በዚህ መሰረትም ባለ ራዕዩ መሪያችን አቶ መለስ ዜናዊ በአዋጅ ይህንን ተግባር የማከናወን ኃላፊነት የተሰጠውን የፌዴራሉን የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት ጊዜውን በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ እያሳለፈ መሆኑን በመግለፅ፤ የሙስና ምንጭ የሆኑትን ተቋማት ለይቶ ጥናትና ክትትል እንዲያደርግ ሲያሳስቡ እንደነበር አይዘነጋም። ኮሚሽኑም ማሳሰቢያውን ተቀብሎ፤ ይህን የሀገርንና የህዝብን ሃብት የመዝረፍ አስነዋሪ ተግባር የሚፈፅምባቸውን የኪራይ

ሰብሳቢነት ምንጮች በበቂ ጥናት ላይ ተመርኩዞ በመለየት ክትትል ሲያደርግ ቆይቷል። ከሁለት ዓመታት በላይ በቆየው ጥናቱና ክትትሉ መሰረትም የትኩረት መስኩን ሲለይ፤ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው መንግስታዊ ተቋማት ውስጥ አንዱ የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን ሆኖ አግኝቶታል። እናም ህግን በማስከበር ስራ ውስጥ የዜጎች ህገ-መንግስታዊ መብት እንዳይነካ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ህጋዊ አሰራሮችን ተከትሎ በቂ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ካሰባሰበ በኋላ፤ ተጠርጣሪዎቹን ሰሞኑን ህግ ፊት አቅርቧቸዋል።

ታዲያ ሃቁ ይህ መሆኑ እየታወቀ ፤ የሀገርና የህዝብ ሃብት ሲዘረፍ አንጀታቸው ቅቤ የሚጠጣ አሉባልተኞች እንደምን 'እነ እገሌ የታሰሩት በፖለቲካ አነሳሽ ምክንያት ነው' እንዳሉ የሚያውቁት እነርሱ ብቻ ናቸው።…ኧረ በዚህ ግልፅ በሆነ ሀገራዊ ህልውናን የማስጠበቅ ጉዳይ ከቶ 'የፖለቲካ ልዩነት ቅብጥርሴ' ማለትን ከቶ ምን አመጣው?…በእኔ እምነት እነዚህ ወገኖች የተሰለፉበት የመንግስትን ስም ከማጥፋት ዘመቻ ባሻገር፤ የኢትዮጵያ ዕድገት የማያስደስታቸውና እንዲደናቀፍ የሚሹም ጭምር ናቸው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም የአንድ ሀገር ዜጋ ሆነው፤ የገዛ ህዝባቸውን ሃብትና ንብረት ለሚዘርፉ ተጠርጣሪዎች የማንቆለጳጰሻ ስም እየሰጡ "እልል በቅምጤ" የሚሉ ነውረኞች ታይተውም ሆነ ተሰምተው ስለማይታወቁ ነው። ግና ይህ የቀን ቅዠታቸው መቼም ቢሆን የሚሳካ እንደማይሆን ማወቅ አለባቸው—የሀገራችን ህዝቦች ጆሮአቸውንና ጊዜያቸውን የሚሰጡት አንድ ጉዳይ በተከሰተ ቁጥር የጥላቻ ድቤን ለሚመቱ ጥላሸት ቀቢዎች ሳይሆን፤ የተመቻቸ የዕድገት ጎዳና በመፍጠር የነገን ብሩህና ፀዳላማ ብርሃናዊ ቀንን እያሳያቸው ላለው ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስታቸው በመሆኑ ነው። በዚህ ብቻ ሳይገቱም ዕድገታቸው ቀጣይ እንዲሆንና ይበልጥ እንዲጠቀሙ የመንግስትን የፀረ-ሙስና ዘመቻ በመደገፍና በቂ ጥቆማ በመስጠት የሰሞኑን ዓይነት ድል ዳግም እንደሚያስመዘግቡ የማጥላላት ሱስ የተጠናወታቸው እነዚህ የልማት ፀሮች ለአፍታም እንኳን ቢሆን ሊጠራጠሩ አይገባም ባይ ነኝ።

ውድ አንባቢዎቼ! እስቲ አሁን ደግሞ እነዚሁ ወገኖች 'መንግስት እስካሁን ምን እየሰራ ነበር፣ ትላንት በሙሰኞች ላይ ለምን አልተነሳም?' ስላሉት የአላዋቂ ሳሚ ጥያቄዎቻቸው ልውሰዳችሁ። እርግጥ የእነዚህ ጥያቄዎች ባለቤቶች ስለ ሀገራችን መንግስት ተግባራት ብዙም ግንዛቤ ላይኖራቸው የሚችሉ የውጭ ዜጎች እንጂ የኢትዮጵያዊያን ናቸው የሚባሉ አይደሉም። ይሁንና ጥያቄዎቹን ያነሱት የራሳቸውን ድብቅ ፖለቲካዊ ሴራ ለማሳካት የሚውተረተሩት የሀገራችን ፅንፈኛ የስልጣን ህልመኞች በመሆናቸው ሃቁን ለመደፍጠጥ መሞከራቸው እምብዛም የሚደንቅ አይደለም። ያው የተለመደው ፀያፍ ምግባራቸው ቀጣይ ክፍል ነውና።

ያም ሆነ ይህ ግን ሁላችንም እንደምናወቀው መንግስት ኪራይ ሰብሳቢነት የሀገራችንና የስርዓቱ አደጋ መሆኑን በማሻማ ሁኔታ ፈርጆ በግልፅ ይፋ ካደረገ ወዲህ፤ ይህን አስከፊ ችግር

ከምንጩ ለማድረቅ በርካታ ተግባራትን ከውኗል–ጥላሸት ቀቢዎቹ እጁን አጣጥፎ ተቀምጦ ነበር ዓይነት የቁራ ጩኸት ለማሰማት ቢሞክሩም። ለነገሩ መንግስት የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ተግባር በሀገራችን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባህል ግንባታ፣ በዘላቂ ዕድገታችን እንዲሁም በህዝቦች ሚዛናዊ ተጠቃሚነት ላይ የሚያሳርፈውን አደገኛ ጠባሳ እንደሚያሳስበው በማውገዝ ብርቱ ትግል ሲያካሂድ መቆየቱ ከማናችንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም። ቀደም ሲል በመግቢያዬ አካባቢ የጠቀስኩትና በአቶ ስዬ ኣብርሃ እንዲሁም በሌሎች ባለስልጣናት ላይ የተካሄዱት ኪራይ ሰብሳቢዎችን የመታገልና ለህግ የማቅረብ ተግባራቱ እንደተጠበቁ ሆነው፤ የሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የኪራይ ሰብሳቢነትን አስተሳሰብ የማያስተናግድ እንዲሆን፣ የተጀመረው የህዳሴና የዕድገት እንቅስቃሴ እንዳይስተጓጎል እንዲሁም ማንኛውም ዜጋ በልማቱ ላይ በሚሳተፈው መጠን ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ መንግስት በርካታ እርምጃዎችን ወስዷል።

ወደ ኋላ መለስ ብለን ጥቂቶቹን ለማስታወስ ያህል ሶስት ዋና ዋና አብነቶችን መጥቀስ ይቻላል– በገጠር፣ በብዙሃን ማህበራትና በሲቪል ሰርቪሱ አሰራሮች ውስጥ። የህዝባችን 85 በመቶ የሚሆነው ህዝብ በሚኖርበት የገጠር አካባቢ፣ ዋነኛ የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጭ ሊሆን የሚችለው የመሬት ባለቤትነት ጉዳይን ለአስተሳሰቡ በማያመች አኳኋን በመመለስ ገጠሩን ከኪራይ ሰብሳቢነት ነፃ ለማውጣት የሚያስችል ወሳኝ ተግባራዊ እርምጃን ገቢራዊ አድርጓል፡፡ በዚህም ኪራይ ሰብሳቢዎች ከመሬት ሽያጭ ያገኙት የነበረውን ጥቅም ለመዝጋት ችሏል፡፡ ሌላኛው ተጠቃሽ ጉዳይ፤ የብዙሃን ማህበራትን (Civil Societies) አስመልክቶ አዋጅ በማውጣት የወሰደው ጠቃሚ እርምጃ ነው፡፡ ምንም እንኳን የብዙሃን ማህበራት ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንቢያ ተቋማት ውስጥ አንዱ መሆናቸው ቢታወቅም፤ አመራሮቹ ማህበራቱን ለኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ በመጠቀም ዴሞክራሲው በጠንካራ መሰረት ላይ እንዳይገነባ የነበሩ አዝማሚያዎች ጎልተው መታየታቸው ግን አልቀረም፡፡ እናም የማህበራቱ መሪዎችም የአመራር ቦታቸውን ከመንግስታዊ ስልጣን ባልተለየ ሁኔታ ኪራይ ለሰብሰብ ሲጠቀሙበት እንዲሁም የአባላቱን መብትና ጥቅም ከማስከበር ይልቅ ለእነርሱ ፍርፋሪ እየሰጡ አባላቱን በመሳሪያነት ከመጠቀም የውድድሩ ክፍፍል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ሲያደርጓቸው ነበር። ታዲያ መንግስት ይህን ችግር ለመፍታት ያወጣው "መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የብዙሃን ማህበራት አዋጅ" የኪራይ ሰብሳቢዎችን ካምፕ እያፈራረሰው ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

በተመሳሳይ ሁኔታም በሲቪል ሰርቪሱ አሰራሮች ውስጥ የኪራይ ሰብሳቢነትን አመለካከትና ተግባር ለመቅረፍ ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል። እርግጥ ካለፉት ሥርዓቶች ይዘናቸው ከመጣናቸው በርካታ ፀረ-ልማትና ፀረ- ዴሞክራሲ ቅሪት አስተሳሰቦች አኳያ በህብረተሰቡ ውስጥ የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰቦች በቀላሉ የሚቀረፉ አይደሉም፡፡ ታዲያ በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ያለው አስፈፃሚ አካል የህብረተሰቡ ውጤት እንደመሆኑ መጠን ከዚህ እሳቤ ይላቀቃል ብሎ ማሰብ

የዋህነት ይመስለኛል። በዚህም ሳቢያ አንዳንድ የሲቪል ሰርቪሱ ሰራተኞች ራሳቸውን የህዝብ አገልጋይ አድርገው የሚመለከቱ ሳይሆን፤ በተገላቢጦሹ እነሱ ተገልጋይ የሆኑ ይመስላቸዋል፡፡ በመሆኑም ኪራይ ሰብሳቢ ረጃጅም እጆቻቸውን በመዘርጋት፤ የመንግስትን ስልጣን ያለአግባብ ለመጠቀም ይሞክራሉ፡፡ በአቋራጭ ለመበልጸግ የጥቅም ትስስር በመፍጠር እንዲሁም የመንግስትን አሰራሮችና ደንቦችን በመፃረር በኪራይ ሰብሳቢነት ጎራ ይሰለፋሉ፡፡ ታዲያ መንግስት ከሙስና እና ከብልሹ አሰራር የፀዳ ሲቪል ሰርቪስን ለመፍጠር ካለው ፍላጎት በመነሳት፤ በእነዚህ ዓይነቶቹ ባለስልጣናቱ ላይ እርምጃ ሲወስድ መቆየቱ የሚዘነጋ አይደለም። ሰሞነኛው የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መስሪያ ቤት ትዕይንት የዚህ የቀጠለ ተግባሩ መገለጫ መሆኑን ለመረዳት ብዙ ምርምር የሚያስፈልገው አይመስለኝም።

እናም መንግስት ከትላንት ጀምሮ እስከ ዛሬ በሙስና እና በሙሰኞች ላይ ተገቢውን እርምጃ በየወቅቱ ሲወስድ እንደነበር ጥላሸት ቀቢዎቹ ሊያውቁት ይገባል። ግና እነዚህ ወገኖች አንድ ትልቅ ጉዳይን መዘንጋት ያለባቸው አይመስለኝም። እርሱም የሙስና ተግባር ባለ ብዙ ስለት ቢላዋ መሆኑን ነው። ድርጊቱ አንድና አንድ የሆነ ወጥ የሆነ ፈርጅ የለውም–ውስብስብና ቀጣይ ትግልን በየጊዜው ይጠይቃል። አንድን የሙስና ክንዋኔ እንደ ሽሮ ፈሰስ በአንድ ጊዜ ጥዶ በማፍላት ወዲያውኑ ማቅረብ አይቻልም። ጥልቅ ጥናትና ክትትልን በተራዘመ የጊዜ ዑደት ውስጥ መውሰዱ አይቀሬ ነው። እናም ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት የተጀመረው የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሙስና ቅሌት ከእዚህ ጉዳዮች አኳያ ተሰልቶ የተሰራ በመሆኑ "ዘግይቷል" የሚለው የአሉባልተኞቹ ሆያ ሆዬ ሚዛን የሚደፋው በራሳቸው ጭንቅላት ውስጥ ብቻ መሆኑን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

ያም ሆነ ይህ ግን ማንም ያሻውን ቢለፍፍ የጉዳዩ ሰለባ የምንሆው ዜጎች በጉዳዩ ዙሪያ የበኩላችንን ድርሻ መወጣት ያለብን ይመስለኛል። እንደሚታወቀው መንግስት ይህን ውስብስብና አፀያፊ ተግባር ያለ ህዝቡ ድጋፍ ብቻውን ሊወጣው አይችልም፡፡ በመሆኑም የኪራይ ሰብሳቢነት አደጋ በዴሞክራሲያችን፣ በልማታችንና በሰላማችን ላይ ያነጣጠረ በመሆኑ ልንኮንነውና ልንታገለው ይገባል፡፡ ለዚህም በቅድሚያ የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብን በጽኑ በማውገዝ፣ በሚደረጉ የጥቅም ትስስሮች ውስጥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተሳታፊ ባለመሆን እንዲሁም በየተቋማቱ ውስጥ የሚገኙ ያልተሰበሰቡ ኪራይ ሰብሳቢ እጆችን አደብ ማስገዛት ይቻል ዘንድ ለሚመለከተው አካል ጥቆማ እየሰጠን በማጋለጥ የዜግነት ግዴታችንንና ኃላፊነታችንን መወጣት ጊዜው የሚጠይቀው ተግባር መሆኑን ለአፍታም ቢሆን መዘንጋት አይኖርብንም፡፡ አማን ያሰንብተን።